*Journal of Afroasiatic Languages, History and Culture (JAAL)*

Volume 11, Number 1, 2022

# SOME NOTES ON THE ROLE OF THE ETHIOPIAN MILITARY REGIMENTS IN THE ANNALS OF INTERACTION OF PEOPLES AND CULTURES (14TH -16TH CENTURIES)

Awegichew Amare Agonafir

**Abstract**

*The historic organization of the medieval Ethiopian military regiments awaits a comprehensive historical study. The present study examines the role of the Čäwa military regiments in stimulating cultural interaction among peoples of diverse identities across regions. The primary sources for the study are royal chronicles of Ethiopian emperors, hagiographies, missionaries' accounts and other contemporary sources. It is found that from the fourteenth to the sixteenth centuries, the Ethiopian Čäwa military regiments had exhibited three major experiences. These are the organization of a mixed ethno-religious and multi-lingual regiments, settlement of the Čäwa in newly integrated regions and remote frontiers and their intermingling with the local population. These long processes of interaction and cultural exchange have stretched to the shifting political geography of the Ethiopian state.*

# በኢትዮጵያ የህዝብና ባህል ትስስር ታሪክ የጦር ሰራዊቱን ሚና የሚመለከቱ አንዳንድ ጉዳዮች (ከ14ኛው እስከ 16ኛው መ.ክ.ዘ.)[1]

አውግቸው አማረ አጎናፍር[2]

**አጠቃሎ**

*የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ጦር ሰራዊት ታሪካዊ አደረጃጀት በታሪክ ምሁራን ዘንድ በበቂ ደረጃ ትኩረት አላገኘም። የዚህ ጥናት አላማም ከ14ኛው እስከ 16ኛው መ.ክ.ዘ. የነበረው የጨዋ የሰራዊት ግምባታ በማጥናት ለባህልና ህዝብ ትስስር ያደረውን አስተዋፅኦ መገምገም ነው። የታሪክ ሰነዶች በተለይም ዜና መዋእሎች፤ ገድላት፤ የአውሮፓውያን ካቶሊክ ሚሲዮኖች ጥናቶችና ሌሎች ሳይንሳዊ የታሪክ ምርምሮች ለጥናቱ መረጃ ምንጭነት ውለዋል። ጥናቱ እንደሚያሳየው ከ14ኛው መ.ክ.ዘ. ጀምሮ የነበረው የጨዋ ሰራዊት ሶስት መሰረታዊ ለውጦች አስተናግዷል። የብዝሀ-ቋንቋ፤ ባህል፤ ሀይማኖትና የትውልድ ቦታ የተውጣጣ የጨዋ ሰራዊት መገንባት፤ አዲስ በተቆረቆሩ ግዛቶችና ድንበሮች የጨዋ ሰራዊት መስፈሩ ከሰፈረበት ማህበረሰብ ጋር በመስተጋብር መተሳሰሩ እና የነዚህ ውጤት የሆነው የንክኪና ትስስር ሂደቱ እየሰፋ በመጣው የሀገሪቷ ዳር ድንበርና ግዛት መስፋፋት ናቸው።*

የኢትዮጵያ የማህበረሰብ ታሪክ ምርምር አንጓዎች ውስጥ የመስተጋብርና ትስስር ታሪክ አንዱ ነው። የታሪክ መረጃዎችን በሳይንሳዊና ሙያዊ መንገድ የተገነዘቡና የተጠቀሙ ምሁራን እንደሚያስረዱት የኢትዮጵያውያን ታሪክ የንክኪ መሆኑን ነው።[3] የባህል፤ የኃይማኖት፤ የቋንቋ፤ የኢኮኖሚ እና ፖለቲካዊ መስተጋብሮች የፈጠሩት መሰናሰን

---

1 መቶ ክፍለ ዘመን። አንድ ምዕተ-አመትን ለማመልከት በአሕፅሮተ-ቃል የተቀመጠ ነዉ።

2 በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የታሪክ መምህርና በኢትዮጵያ የህዝብና ባህል ትስስር ታሪክ ተመራማሪ።

3 Shiferaw Bekele (1990), "Reflection on the Power Elites of the Wäräšeh Mäsfenate (1786-1853)," *Annales d'Ethiopie*, XV, pp. 157-179; Brian J. Yates (2002) "Invisible Actors: The Oromo and the Creation of Modern Ethiopia (1855-1913)," PhD Dissertation, Department of History, University of Illinois; Idem (Fall/Winter 2010-2011), "Acculturation in the Däga: Local Negotiations in Amhara/Oromo Relations," *International Journal of Ethiopian Studies*, VI, 11; Heran Serke Berhan (2002), "Building Bridges, Drying Bad Blood: Elite Marriage, Politics and Ethnicity in the 19th and 20th Century Imperial Ethiopia," PhD Dissertation, Department of History, Michigan State University; Awegichew Amare (2019), "Yä-Oromo Həzb Tarikən Yätänətärasu Yätərəkət Täqarənowoč Lämaläzäb Yähəzbəna Bahəl Mästägabər Tarik Mərmər Mina," [The Role of A History of Interaction and Integration of People and Culture to Relax Conflicting Narratives in Oromo History] *Journal of Afroasiatic Languages, History and Culture,* VIIII, II, pp. 221-245.

ኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሰረት ያለው አሰባሳቢ ማንነት መሆኑን አስረጅም ነው። ይህ የልውውጥ ታሪክ ለረጅም ዘመናት የተደረገ፤ የተለያዩ ተዋናዮች የተሳተፉበትና እጅግ ውስብስብ መልኮች፤ ሂደቶችና ውጤቶች ያሉት ነው። የአስተዳደር መዋቅሮችን በመዘርጋት ዘለግ ያለ የመንግስት ታሪክ ያላት ኢትዮጵያ ያልተቋረጠ፤ የተመዘገበ፤ የግዛት አንድነትን እና የህዝብን ህልውና የጠበቀና ያስቀጠለ የመስተጋብር ታሪክ አላት። የተለያዩ ሃይማኖቶች፤ ቋንቋዎች፣ ባህል፣ እምነት፣ አካባቢ፣ እና የፖለቲካ አመለካከት ያላቸውን ህዝቦች ስርአት በማስገባት ማስተሳሰር በሺህ አመታት የሚቀመጥ ግዙፍ የታሪክ አካል ነው።

የትስስር ሂደቶችን ለመተለም፤ ስርአት ለማበጀትና ተቋማዊ ለማደረግ ጉልህ ሚና የነበራቸው አስተዳደራዊ፤ ርዕዮተ-አለማዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊና ወታደራዊ አደረጃጀቶችና ስልቶች ነበሩ።[4] አላማውም በተለዋዋጩ የኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የሚኖሩ ማህበረሰቦችን ሊያስባስቡ የሚችሉ የመስተጋብር መረቦችን በመዘርጋት የጋራ ማንነትን እና የአንድ ሀገር ልጅነትን ማዕከል ያደረገ ሃገርን መገንባት ነበር። በዚህ ረገድ መንግስት፤ የኃይማኖት ተቋማት፤ እና የማህበረሰቡ ሀገር-በቀል አደረጃጀቶች በግልና በትብብር ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

በዚህም የተነሳ የኢትዮጵያን የትስስር ታሪክ በፓሊቲካ ልሂቃን፣ ካህናት፣ የእስልምና መምህራን፣ በነጋዴው፣ በወታደሩ፣ እና በማህበረሰቡ በተፈጠሩ ስርአታዊ የግንኙነት መረቦች የተደረጉ መስተጋብሮች ውጤት ያደርገዋል።[5] በታሪክ ፀሀፍት ዘንድ ለመስተጋብር ታሪክ እና የአንድነት አምዶች የተሰጠው ትኩረት እምብዛም ቢሆንም የፖለቲካ ትስስሮች በአንፃራዊነት በተሻለ ስፋትና ጥልቀት ተጠንተዋል። የክርስትና እና እስልምና ታሪክ ጥናቶች በተለያየ ደረጃ የተዋናዮቹን፤ የተቋማቱንና የተከታዩን ሚና ያስረዳሉ።[6] ይሁንና የወታደራዊ ታሪክ ምርምር ተጨማሪ ትኩረት ይጠብቃል። ከጦር ሜዳ ውሎ እና የፖለቲካ ውጤቶች ዘገባ ባለፈ የኢትዮጵያ ታሪካዊ የጦር ሰራዊት የማህበረሰቦችን ትስስር እንዳነፀ እና እንዳፀና ማጥናት ወሳኝ የጥናት መስክ ነው።

የኢትዮጵያን የጦር ሰራዊት ታሪክ ለማጥናት ውስብስብ ተግዳሮቶች አሉ። የታሪክ መረጃዎች ውስን ናቸው። በፖለቲካ ዘገባ ላይ የሚያተኩሩት ሰነዶችን በመጠቀም

4 Awegichew Amare (2021), "The Imperial Traditions of the Ethiopian State and the Oromo Factor (XIV-XVIII Centuries)," PhD Dissertation in History, Addis Ababa University, pp. 136-158.

5 ዝኒ ከማሁ።

6 የክርስትና ሀይማኖትን መስፋፋትና ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ያለዉን ታሪካዊ ትስስር በተመለከተ ይህንን ተመልከት። Taddesse Tamrat (1972), *Church and State in Ethiopia*, 1270-1527 (London: Clarendon Press). የእስልምና ታሪክ፤ ሰነዶችና ምሁራን ጥናቶችን በተመለከተ ዋቢ መፃህፍት ላይ የተደረገ ጥናትን ለማግኘት ይህንን ተመልከት። Hussein Ahmad (1992), "The Historiography of Islam in Ethiopia." *Journal of Islamic Studies*. III, I, pp. 15-46).

የወታደራዊ አደረጃቶችን፣ ስብእናና ኩነቶችን በጊዜና በቦታ ለመረዳት አዳጋች ነው። የጦር ሜዳ ውሎ ዘገባዎች በዋናነት ከጦርነቱ ዝግጅት፣ የጦር ጀግኖችና ተሸናፊዎች ላይ ትኩረት ስለሚያደርጉ ነባራዊውን ስርአታዊ፣ ተቋማዊ እና መዋቅራዊ አቋምን በበቂ ደረጃ ለመፈተሽ እና ውስብስብ ምስሉን ማስቃኘት ያዳግታል። ይህም ጥናት ይህንን ውስንነት በመረዳት ያሉትን ውስን ግን ጠቃሚ የታሪክ ሰነዶች በመጠቀም የጦር ሰራዊቱ ለመስተጋብር ታሪክ ያለውን ሚና ያስረዳል።

የኢትዮጵያ የጦር ሰራዊት አደረጃጀት መነሻ ዘለግ ያለ ታሪክ አለው። የታሪክ ምንጮች እንደሚጠቁሙት የአክሱም ነገስታት ከተለያዩ ነገዶች የተወጣጡ፤ በየደረጃው የማዕርግ ስም የተሰጣቸው የጦር ሰራዊት ክፍሎች ነበሯቸው። አፄ ኢዛና (320-360?? እ.ኤ.አ.[7]) ዳከወን፤ ደመዋ፣ ፍልሃ፣ ሃለን፣ ሀራ፣ ላከን፣ ማገሮ፣ መጢን፣ ሰበረት፣ እና ስራ የተሰኙ ክፍል ጦሮች እንደነበሩት ይጠቀሳል። ተቀዳሚ ግዳጃቸም ግዛትን የማስፋት፤ የንግድ መስመሮችን የመቆጣጠርና የመጠበቅ እና ግብር የመቅረጥ ሲሆን ከገቢው የሚገኘው ሃብትም ሰራዊቱን በቁጥር፣ በመሣሪያ፣ እና በአቅርቦት ለመደገፍ ይውል ነበር።[8] ከሰባተኛው መ.ክ.ዘ. ከጀመረው የአክሱማዊያን የኢኮኖሚ ኢምፓየር ወድቀት በኋላ በ12ኛውና 13ኛው መ.ክ.ዘ. በላስታ (ወርወር) የነገሱት የዛጉዌ ስርወ-መንግስት የኢትዮጵያ ነገስታት ስለነበራችው የጦር ሰራዊት ሁኔታ በተመለከተ በቂ የታሪክ ሰነዶች ማግኘት አልተቻለም። ይሁንና የመንግስት ስርአታቸው ከአክሱማውያን ጋር በነበራቸው ትብብር እና ፉክክር ውጤት እንደሚሆን በባህል፣ ስነ-መንግስት፣ ስነ-ህንፃና ሀይማኖት የታየው ቀጣይነት አስረጂ ነው።[9] እንደ ቀደምቶቻቸው ወታደራዊ የመንግስት ስርአት ይኖራቸዋል ተብሎ ባይታሰብም ከጦር ሰራዊት ግንባታ የራቁ እንዳልነበሩ በላሊበላ ዙሪያ የተደረጉ አንዳንድ የቅርብ ጥናቶች ይጠቁማሉ።[10]

በጦር ሰራዊቱ ግንባታ የኢትዮጵያን የመስተጋብር ታሪክ ሊቀይር በሚችል መልኩ ጉልህ ለውጥ የተደረገው ከ14ኛው መ.ክ.ዘ. ጀምሮ ነበር። የሰራዊቱ ክፍሎች በአዲስ መልክ የተደራጁት በአፄ አምደ ፅዮን (1314–44 ዓ.ም.) ዘመን ነበር። በዘመኑ ኢትዮጵያ አራት አይነት የወታደር አደረጃጀቶች ነበሯት። አንደኛው የንጉሰ-ነገስቱ ቋሚ ሰራዊት ነው። ሁለተኛው በተዋረድ በጦር መሪዎች የሚመራ ቋሚ ሰራዊት ነው። በተለየ ሁኔታና ቦታ የሚሰፍር የግዛት ጠባቂ ሰራዊት ሶስተኛው ክፍል ነው። የመጨረሻውና አራተኛው ኢ-

7 ይህ ጥናት የአዉሮፓዉያን የዘመን አቆጣጠር ይጠቀማል። እ.ኤ.አ. በሚል ተመላክቷል።

8 Merid Wolde Aregay (1997), “Military Elites in Medieval Ethiopia,” *Journal of Ethiopian Studies*, XXX, I, p. 37.

9 David W. Phillipson (2004), “The Aksumite Roots of Medieval Ethiopia,” *Journal of British Institute in East Africa*, pp. 77-89.

10 Marie-Laure Derat (2020), "Before the Solomonids: Crisis, Renaissance and the Emergence of the Zagwe Dynasty (Seventh–Thirteenth Centuries)" in Samantha Kelly (ed), *A Companion to Medieval Ethiopia and Eritrea* (Netherlands, Leiden: Brill Publishers), p. 49.

መደበኛ ሰራዊት ነው። በአፄ አምደ ፅዮን ብዛትና አቅም ያለው ሰራዊት የንጉሰ-ነገስቱ እንዲሆን ተደርጎ ሲደለደል፣ ይህም ስርዓት ለሁለት መቶ አመታት ያህል ቀጥሏል።[11] ይህ አዲስ የጦር ሰራዊት ስርአት ሶስት መሰረታዊ ለውጦችን አስከትሏል። እነዚህም ከብዝሃ-ቋንቋ፣ ባህል፣ ሀይማኖትና አካባቢ የተውጣጣ የጨዋ ጦር ሰራዊት ግንባታ፤ አዲስ በተቆረቆሩ ግዛቶች የጨዋ ጦር ሰራዊት የማስፈር፤ እና የግዛት መስፋፋት ናቸው።

ከላይ የተጠቀሱት ለውጦች ውስብስብና ለረጅም አመታት የተደረጉ የታሪክ ሂደቶች ሲሆኑ እርስ በርስም የተሳሰሩ ነበሩ። የጦር ሰራዊቱ የሃገሪቱን ዳር ድንበር ከማስፋፋትና ወደ ግዛቱ የተጠቀለሉትን የግዛት አንድነትን ከመጠበቅ በተጨማሪ በተቀያያሪ የግዛት ስፋት ውስጥ የሚኖር ህዝቦችን ደህንነትና አንድነት የመተለምና የማስጠበቅ ኃላፊነትን ሲወጣ ኖሯል።

ለተስፋፊና ወራሪ ሃይሎች መተላለፊያ የሆኑ ግዛቶችን እንዲሁም ከምስራቅ ቆላማ ስፍራዎች ወደ ምዕራቡ አርሶ አደር መኖሪያ ከፍተኛ ተራሮች የሚደረጉ ተስፋፊና አደገኛ እንቅስቃሴዎችን ለመቆጣጠር ሲባል በተደረገ እንቅስቃሴ ለተጨማሪ የግዛት መስፋፋት ምክንያት ሆኗል።[12] በሂደት እየሰፋ ከመጣው ግዛትም የኩሽቲክ፣ ሴሜቲክ፣ ናይሎቲክና፣ ኦሞቲክ ቋንቋ ተናጋሪዎችን፣ የክርስትና፣ እስልምና፣ አይሁድና ሌሎች እምነት ተከታዮችን መሰተጋብር ከመጠበቅና፤ ማስቀጠልና ማሳለጥ አንፃር በ14ኛው መ.ክ.ዘ. የተቀየሰው የጦር አደረጃጀት ልዩ ቦታ ይሰጠዋል።

**ትስስርን ያማከለ የጨዋ ጦር ሰራዊት ግንባታ**

ከ13ኛው መ.ክ.ዘ. ጀምሮ ያለውን የሰራዊቱን ባህላዊና ማህበረሰባዊ ምንጭ መፈተሽ የአደረጃጀቱን ህዝባዊ መሰረትና ብዝሃ-ማንነት ለመረዳት ያግዛል። አፄ ይኩኖ አምላክ (1270-1285 ዓ.ም.) የተለያዩ ብሄርና ኃይማኖት የነበራቸው ወታደሮችን ያሰባሰበ ሲሆን በተለይም የሸዋ ተወላጅ ሰራዊቱ "ሰባቱ ጉዳም" በሚል ስያሜ ይታወቃል። ዘመኑን ያጠኑት የታሪክ ምሁራን በተለይም ታደሰ ታምራትና መርዕድ ወልደአርጋይ እንደሚጠቁሙት የይኩኖአምላክ ሰራዊት ስያሜ ሸዋ ውስጥ ከሚገኙ የቦታዎች ስም ጋር

11 በዚህ የጦር አደረጃጀት ላይ በቂ መረዳት ለማግኘት የአፄ አምደፅዮንን ዜና መዋእል ይመልከቱ፡- G.W.B. Huntingford (ed/tran) (1965) *The Glorious Victories of Amda Seyon* (Oxford: Clarendon Press). See also Richard Pankhurst and Andreu Martinez d'Alos Moner (2007), "Military Units," *Encyclopaedia Æthiopica*, V, pp. 430-433.

12 አርሶ አደሩን፣ ነጋዴዉን፣ እንዲሁም በተለያዩ ሙያ በቋሚነት ተሰማርተዉ በደጋዉ፤ ወይናደጋ እና ከፍተኛ ተራሮች የሚኖረዉን ህዝብ ከቆላማ ስፍራዎች ከሚነሱ ሽፍቶች ጥቃት ለመጠበቅ የተደረገ የመከላከል የጦር ስልት እንዴት ወደ ማጥቃትና የሽፍቶቹን ምንጭ ግዛቶች ወደመቆጣጠር እንዳደገ መርእድ በጥናታቸዉ አስረድተዋል፤ Merid Wolde Aregay (1974), "Population Movements as a Possible Factor in the Christian-Muslim Conflict of Medieval Ethiopia," *Symposium Leo Frobenius; Perspectives of Contemporary African Studies*, pp. 266-281.

የተገናኘ ሲሆን ሰባቱ ጉዳም የተባሉትም ወግዳ መለዘይ፣ ደምቢ ደበራይ፣ ሙገር እነደዛቢ፣ ውጅ እናጋሪ፣ ወረብ እንጋፌ፣ ስላልሽ እናጋፌ እና ምዋል አውጃጃይ ናቸው፡፡[13] መለዛይ በሚል የተጠቀሰው የሰራዊት ስም መለሳይ ከተባለው የአዳልና ሃረር ሙሰሊም ሰራዊት ጋር ይመሣሠላል። ይህ ስያሜ በ16ኛው መክ.ዘ የሶማሌ ፈረሰኛ ጦር ስያሜ ሆኖ ሲያገለግል በአፄ ሰርፀ ድንግል (1563-1597 ዓ.ም.) ዜና መዋዕል ላይ የንጉሱ ተባባሪ የሙስሊም ሰራዊት ሆኖ ተጠቅሷል፡፡[14] የሃደያው ገራድ አዜ ሰራዊት ሆኖም ተጠቅሰዋል፡፡[15]

በዘመኑ ከሸዋ በተጨማሪ ከአማራ፣ አገው እና ትግሬ የተመለመሉ የሰራዊት ክፍሎች በቆላማና ከፍተኛ ተራሮች መካካል ሰፍርው የአርሶ-አደሩን ደህንነት ይጠብቁ ነበር። ከክርሰትና ኃይማኖትና ባህላዊ መሠረት ካላቸው አካባቢዎች ከተወጣጣው ሰራዊት በተጨማሪ ይኩኖአምላክ የሙስሊም ሰራዊት ክፍል እነደነበረውና ይህም ፈርሰኛ ክፍለ-ጦር እነደነበር ተጠቅሷል፡፡[16] የማያ እና ዘላን እንዲሁም የጋፍት ሰራዊት እንደነበርውም የታሪክ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡[17] ይህ ሰራዊትም  የክርስቲያኑ ግዛተ-አፄ ከሚፎካከሩትና የሸዋ ከፍተኛ ቦታዎች ለመቆጣጠር ከሚተጉት ከዳሞት ግዛተ-አፄ እንዲሁም ከኢፋት ሱልጣኖች ጋር ብርቱ ተጋድሎ አድርጎ የሀገሪቷን ድንበር አስፋፍቷል። በ13ኛው መ.ክ.ዘ. ሁለተኛው አጋማሽ የኢትዮጵያ ግዛት የሸዋ ከፍተኛ ተረሮችን ይዞ የአሸዋ ወንዝ በስተሰሜን ድረስ ሊስፋፋ ችሏል፡፡[18] በተፎካካሪ ሃይሎች ሊደርግ ይችላል ተብሎ የሚጠበቅን ጥቃት ለመመከት የታቀደው የመከላከል ዕቅድ በሂደት ሌሎች ግዛቶችን ወደማጠቃለል አድጎ በተያዙት ቦታዊችም ሰራዊት  ማስፈር የተለመደ ይዞታን የማፅናት፤ አስተዳደራዊ፣ ባህላዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተቋማትን የመመስረቻና ማስፋፊያ መንገድ ሆነ፡፡[19]

14ኛው መ.ክ.ዘ. በጦር ሰራዊት ግንባታ ታሪክ አዲስ ምዕራፍ የከፈተ ነበር። በዘመኑ ገናና ጦረኛ መሪ አፄ አምደ ፅዮን የተደራጀው የጦር ሰራዊት በንጉሱ ዜና መዋእልም ተጠቅሷል። በዚህ ለነገስታቱ በተፃፈ የመጀመሪያው ዜና መዋእል መሰረት ሶስት የጦር ሰራዊት ክፍሎች ተገልፀዋል። አንደኛው ሰራዊቱ በተመለመሉበት አካባቢ የተሰየሙ

---

13 Taddesse Tamrat (1972), *Church and State in Ethiopia…..*,p. 119; Merid Wolde Aregay (1997), "Military Elites in Medieval …..", p. 41.

14 Carlo Conti Rossini (ed/tran) (1961-62), *Historia regis Sarṣa Dengil (Malak Sagad). Accedit historia gentis Galla, curante I. Guidi*, II vols., CSCO II ser., III (Paris, 1907), repr. as CSCO XX-XXI, SAe III–IV (Louvain) (text), p. 16.

15 ዝኒ ከማሁ (text), ገፅ. 40-41.

16 Taddesse Tamrat (1972), *Church and State in Ethiopia…..*,p. 126.

17 Merid Wolde Aregay (1971), "Southern Ethiopia and the Christian Kingdom 1508- 1708, With Special Reference to the Galla Migrations and their Consequences," PhD Dissertation, Department of History, SOAS, University of London, p. 136.

18 Taddesse Tamrat (1972), *Church and State in Ethiopia…..*,p. 120.

19 Merid Wolde Aregay (1974), "Population Movements…...", pp. 266-281.

ክፍሎች ናቸው። ሁለተኛው ባላቸው የጦር ብቃት መሰረት የወታደራዊ ማዕረግ የተሰጣቸው የጦር ልሂቃን (elite force) ሲሆኑ ሶስተኛው ባነገቡት የጦር የመሳሪያ አይነት የተደለደሉ ናቸው።[20]

የአፄ አምደ ፅዮን ጦር ሰራዊት ከተለያዩ ከተማዎች፣ ግዛቶችና አካባቢዎች የተውጣጣ ነበር። ለአብነትም ከአምሃራ፣ ሸዋ፣ ጎጃም፣ ዳሞት፣ ሀድያ፣ ሰቀልት፣ ጎንደር፣ ጋፋትና ናራ ናቸው። ፈረሰኞቹ ደግሞ የቀኝና የግራ ተብለው ተከፍለዋል። ይህ ሊታወቅ የቻለውም ወታደሮቹ ለንጉሱ አክብሮትና ጀግንነት መገለጫ በዘፈኑት የሙገሳ ዘፈን ነበር።[21]

በዚህ መረጃ መሰረት ንጉሱ በወረራ የተቆጣጠራቸውም ግዛቶች ስም ተጠቅሶ ይገኛል። ለታከሪ ጥናት ፋይዳ እንዳላቸው የተገመገሙት እነዚህ የሙገሳ ዘፈኖች በአፄ አምደ ፅዮን ዘመን የነበረውን የኢትዮጵያ የግዛት መጠንና ወደ መንግስትዊ መዋቅር እና ስርአት የተካተቱ ማህበረሰቦችን፣ እንዲሁም ባህላቸውን፣ ቋንቋቸውን እና ሀይማኖታቸውን ለመረዳት ያግዛል።[22] ወደ ኢትዮጵያ ግዛተ-አፄ የተጠቃለሉ ግዛቶችም አዳዲስ ምልምል ሰራዊት አባላት የተለያዩ የጦር ክፍሎችን እንዲቀላቀሉ ይደረግ ስለነበረ የሰራዊቱን አካባቢያዊ ምንጭ ያስረዳናል። የእናሪያ፣ ሃድያ፣ ኢፍትና ሌሎች የደቡብ ግዛቶች ውስጥ የነበሩ ወታደሮች የመንግስትን የጦር ሰራዊት ተቀላቅለዋል። ይህም የባህል፣የቋንቋና ኃይማኖት ልውውጥ ከመፍጠሩ ባሻገር የክርስቲያኑን ግዛተ-አፄ ጦር ሰራዊት ቁጥር፤ አቅም፤ የውጊያ ስልትና የጦር መሳሪያ አይነት ሊያሻሽል ችሏል።

ግርማ፣ የአማርኛ ታሪካዊ ሰዋሰውን በተመለከቱበት ጥናታቸው ላይ ከብሩስ የቦድሊያን ስብስብ ከነገስታቱ የሙገሳ ግጥሞች መካከል ለአፄ አምደፅዮን፤ አፄ ዳዊት (1375-1404)፤ አፄ ይስሀቅ (1413-1428)፤ አፄ ዘርአያዕቆብ (1434-1468)፤ እና አፄ ገላውዴዎስ የተገጠሙትን አካዋቸዋል፡፡[23] እነዚህ ግጥሞች ሀንቲንግፎርድ ባሳተሙት የንጉሱ ዜና መዋዕል የእንግሊዝኛ ትርጉምና አርትኦ ላይ በእንግሊዝኛ ቀርበዋል፡፡[24]

20 G.W.B. Huntingford (ed/tran) (1965), *The Glorious Victories of Amda Seyon…..*, p. 81.


21 ለነገስታቱ የተዜሙ የሙገሳ ግጥሞችን በዚህ ጥናት ትንታኔ ተሠጥቶበታል፤ Ignazio Guidi (1889), "Le Canzoni Geez-Amarina in onore di re Abissini," *Rendiconti della Reale Accademia dei Lincei*, series IV, V (Roma), pp. 53-66. ግጥሞቹ ታሳቢ ያደረጉትን አላማ በተመለከተ ምሁራዊ ትንታኔን ተመልከት፤ André Caquot (1957), "La royauté sacrale en Éthiopie," *Annales d'Ethiopie*, II, pp. 205-218.

22 አፄ አምደ ፅዮን የተሞገሱበት ግጥሞች ከጀምስ ብሩስ የቦድሊያን ስብስብ ተወስዶ ከዜና መዋእሉ ጋር ቀርቧል፤ G.W.B. Huntingford (ed/tran) (1965), *The Glorious Victories of Amda Seyon…..* p. 132.

23 Girma A. Demeke, *Grammatical Changes in Semitic: A Diachronic Grammar of Amharic* (Trenton NJ: Africa World Press, 2014), pp. 262-272.

24 G.W.B. Huntingford (ed/tran) (1965), *The Glorious Victories of Amda Seyon…..*,ገፅ. 129-130.

የአማርኛ ግጥሞቹ በዘመኑ አማርኛ የተፃፉ ስለሆኑ የእንግሊዝኛዉን ትርጉም በማነፃፀር በተሻለ መረዳት ይቻላል፡፡



ሓርበኛ፡ ዓምደ፡ ፅዮን፡፡
መላላሽ፡ የወሰን፡፡
ወኻ፡ እንደመስን፡
መላላሽ፡ የወሰን፡፡
ከወጅ፡ ዜብዳርን፡፡
ይውረድ፡ አድርገኸው፡ ትግሬውን፡፡
ከወጅ፡ ዜብዳርን፡፡
ከገንዝ፡[25] ጠጠን፡፡
ምን፡ ቀረኸ፡ በወሰን፡፡
ከባሊ፡ አሊን፡፡
ከደዋሮ፡ ኄደራን፡፡[26]
ከፈጠጋር፡ ዜላርድን፡፡

25 ከወጅ በስተ ምእራብ ይገኝ የነበረ ግዛት፡፡
26 በዜና መዋእሉ ሀይደራ በሚል ይቀመጣል፡፡

ኬፋት፡ አምበልአቦከርን፡፡
ከግድም፡ የዊሳይን፡፡
ከአንጎት፡ ዣን፡ አሞራን፡፡
ከአገው፡ አቤት፡ አዠርን፡፡[27]
ከትግሬ፡ ነገደ፡ ክርስቶስ፡ ይውረድ፡፡
አደረግኸው፡ ገንዙን፡፡
እንዲሰራ፡ ዳውዣውን፡፡
ማን፡ ቀረህ፡ በወሰን፡፡
አላጸፋኸው፡ ፊቱን፡፡
አላስማረኸው፡ ልጅ፡ ምሽቱን፡፡
ከጎዠም፡ ዠን፡ ኸምርን፡፡[28]
ከጋፋት፡ አወላሞን፡፡[29]
በዳሞት፡ ሞት፡ ለሚን፡፡[30]
ማን፡ ቀረህ፡ በወሰን፡፡
ያላጸፋኸው፡ ፊቱን፡፡
አላስማረኸው፡ ልጅ፡ ምሽቱን፡፡
ሓርበኛ፡ ዓምደ፡ ፅዮን፡፡
መላላሽ፡ የወሰን፡፡
ዓምደ፡ ፅዮን፡ ስም፡ ይዘራ፡፡
በወጅ፡ እስከ፡ በጥርአሞራ፡፡
ቃራ፡ ይነሰንስ፡ ቃራ፡ እንደ፡ ጭራ፡፡
በወንዶች፡ ገረገራ፡፡
በሀድያ፡ እስከ፡ ጉዴላ፡፡
በባህር፡ እስከ፡ ኤርትራ፡፡

27 አቤት አዣር፤ በአገው የተለመደ ማእረግ ሊሆን ይችላል፡፡ G.W.B. Huntingford (ed/tran) (1965), *The Glorious Victories of Amda Seyon.....*, p. 133.

28 የተለመደዉ የጎጃም ገዢ ማእረግ "ነጋሽ" ነው፡፡

29 አዋላሞ ማእረግ ሊሆን ይችላል፡፡ ጋፋትና ዳሞት በ14ኛው መ.ክ.ዘ. የጎጃም ደቡባዊ ክፍልን ይሸፍናሉ፡፡

30 ሞታላሚ የሚለው በአቡነ ተክለ ሀይማኖት ገድል ላይ በስፋት የሚታወቀው የዳሞት ገዢ ጀምሮ የማእረግ ስም የነበረ ነው፡፡ ይህንን በዝርዝር ለመረዳት እነዚህን ጥናቶች ተመልከት፤ Ernest Alfred Wallis Budge (1906) (ed./tran), *The Life and Miracles of Takla Hâymânôt in the Version of Dabra Libânôs* (London: privately printed for Lady Meux)፤ Daniel Kibret (2011), *ʾItyopyawiw Surafi, Yä-abunä Täklähaymanot Yähəyəwot Tarikəna Asətäwaṣo* (The Ethiopian *Sur'afi*, The Biography and Achievements of *Abunä* Täklähaymanot) (Addis Ababa).

ዓምደ፡ ፅዮን፡ ስም፡ ይዘራ፡፡[31]

ባላቸው የጦር ብቃት መሰረት ወታደራዊ ማዕረግ የተሰጣቸው የጦር ልሂቃን የተለያየ ስያሜ ያለውና በንጉሱ የቅርብ ጓደኛ ወይም የቤተሰብ ትስስር ባላቸው የጦር አዛዦች ይመሩ ነበር። ተኩላ፣ ቀስተ ንህብ (የንብ ቅስተ)፣ ኮረም (ፈረሰኛ) በመባል ጥንካሬያቸውንና የተለያ ብቃታቸውን በሚያሳይ መልኩ የሚጠሩ ነበሩ።[32] በተለይ የእግረኛው ጦር እንደ ንስር ተዋጊ፣ እንደ ዱር ፍየል ተወርዋሪ፣ የእግሮቻቸው እንቅስቃሴ ከሚንከባለል ድንጋይ ጋር የሚመሳሰል፣ ድምጻቸው እንደ ውቅያኖስ ወጀብ የሚያጉረመርም እንደነበር ተዘግቦ ተቀምጧል።[33] ይህ የጦር ክፍል በተለያዩ ቦታዎች ስልጠና ይወስድ ነበር።[34]

በሚያነግቡት የጦር መሳሪያ የሚጠሩትም የተለያየ ስያሜ አላቸው። ጸዋርያነ ወርመት (ጦር ተሸካሚ?)፣ ጸዋርያነ ወርመት ዐቢያን (ረጃጅም ጦር የሚይዙ)፣ ጸዋርያነ አሳይፍት (ባለ ጎራዴዎች)፣ ሰራዊት እለ ይጸውሩ ወልታ (ባለ ጋሻ)፣ ወዘተ ነበሩ።[35] ከተለያዩ ባህል፤ ቋንቋና፣ አካባቢዎች የተወጣጡ ወታደሮች መኖራቸው ሃገር በቀል የጦርነት መሳሪያዎችና የውጊያ ስልቶች ልምድ ልውውጥ ለማድረግ አመቺ ሁኔታ ፈጥሯል።

በቀስተኛ፣ ፈረሰኛ እንዲሁም እግረኛ ውጊያ ስልቶች የአካባቢውን ተሞክሮ በማዳበል ጠንካራ ሰራዊት መገንባት ተችሏል። ጦር፣ ጋሻና ቀሰት በወቅቱ መሰረታዊ ትጥቅ ነበሩ። ይሁንና ከተለያዩ አካባቢዎች የመጡ ወታደሮች የራሳቸውን የጦር መሳሪያ ይጠቀሙም ነበር። ለአብነትም የማያ እና ዘላን ነገዶች በመርዘኛ ቀስቶቻቸው ዝነኛ ነበሩ። የከብቶች መንጋ በመጠቀም የጠላትን ጦር የመበተንና ምሽግ የመስበር ስልትም የተካኑም ነበሩ።[36]

---

31 ለአፄ አምደፅዮን በአማርኛ ከተገጠሙ የሙገሳ ግጥሞች መከካል (ምንጭ፡- Girma A. Demeke, *Grammatical Changes in Semitic: A Diachronic Grammar of Amharic* (Trenton NJ: Africa World Press, 2014), pp. 262-263).

32 G.W.B. Huntingford (ed/tran) (1965), *The Glorious Victories of Amda Seyon*…..,p. 81; Taddesse Tamrat (1972), *Church and State in Ethiopia*…..,pp. 90-94; Richard Pankhurst and Andreu Martinez d'Alos Moner (2007), "Military Units", p. 430.

33 G.W.B. Huntingford (ed/tran) (1965), *The Glorious Victories of Amda Seyon*…..,p. 81; Richard Pankhurst and Andreu Martinez d'Alos Moner (2007), "Military Units", p. 431.

34 Richard Pankhurst and Andreu Martinez d'Alos Moner (2007), "Military Units", p. 430.

35 ዝኒ ከማሁ።

36 Merid Wolde Aregay (1971), "Southern Ethiopia and the Christian Kingdom….., p. 96.

በየግዛቱ የውትድርናና ጦረኝነት ባህል እያደገ በመሄዱ ለዚህ መሰል ልህቀት ጉልህ አስተዋፅኦ ነበረው።[37]

ከ14ኛው መ.ክ.ዘ ማብቃት በኋላ በጠንካራ ጦር ሰራዊት የሚጠበቅ የተማከለ የፖለቲካ አስተዳደር ለመገንባት ተሞክሯል። በዘመኑም ብዝሀ-ባህል፣ ቋንቋና አካባቢያዊ ማንነት ያላቸው ወታደሮችን የመመልመል ስርዓት እንዲቀጥል ተደርጓል። በአፄ ዘርአ ያዕቆብ (1434-1468) ዜና መዋእል ላይ እንተጠቀሰው ንጉሱ ለጨዋ ሰራዊታቸው እጃቸውን በማውለብለብ ሰላምታ ሲያቀርቡ ወታደሮቻቸው በዕልልታና በፉጨት በየአካባቢያቸው ቋንቋ ይዘፍኑና ያሞግሱት እንደነበር ተጠቅሷል።[38] በአንድ ማህበራዊ ማንነት ማዕካላዊነት ሰራዊቱን የማደራጃት ሰርአት እንዳልነበረ አመላካችም ነው።

ባለብዝሀ ባህል ጦር ሰራዊት የማደራጀት ባህል የበር ሰአዳዲን (አዳል) መሪዎችም ዘንድ የተለመደ ነበር። በዚህ ረገድ መሃፉዝ እና መሃመድ ኢማም አህመድ ኢብራህም ፣ የክርስቲያኑን መንግስት ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና፣ የጦር ሰራዊት አደርጃጀት የሚመስል ስርዓት ዘርግተዋል። ይህም ለረጅም አመታት በተደረገ የኢኮኖሚና ወታደራዊ ፉክክርና ትብብር የመጣ የመስተጋብር ውጤት እንደሆነ መረዳት ይቻላል። የተለያዩ ብሄር፣ ቋንቋና፣ የትውልድ ቦታ ያላቸውን ወታደሮች በአንድ ዕዝ ስር በማካተት ገናና የነበረ ሰራዊት መገንባት ችለዋል። አህመድ ኢብራሂም ከሙስሊምና ክርስቲያኖች፣ ከአርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች የተወጣጣ ሰራዊት ነበረው። በቀስትና ጦር የተካኑትን የመለሳይ ተዋጊዎች፣ የሱማሌ ወታደሮች፣ ሀርላዎች፣ ሀድያዎችን እንዲሁም አደጋ ያደርሱ የነበሩ ሽፍቶችን ያካተተው ሰራዊት በ16ኛው መ.ክ.ዘ. የመጀመሪያ አጋማሽ የኢትዮጵያን ግዛተ-አፄ የጨዋ ሰራዊት በጦር ሜዳ መርታት እንደቻለ የበር ሰአዳዲን ወረራን ከ1526 እስከ 1537 ዓ.ም የዘገበው የመናዊ ሽአባዲን አህመዲን አብደል ቃድር ሳሌም ቢን ኡትማን ወይም አረብ ፈቂህ ፅፏል።[39]

የክርስቲያኑ መንግስት ሙስሊም ወታደሮች እንደነበሩት ሁሉ የበር ሰአዳዲን ጦር ሰራዊት ከሙስሊም ማህረሰብ ብቻ የተወጣጣ አልነበርም። የበር ሰአዳዲን መሪዎች ክርስቲያን ወታደሮች አብዛኛዎቹ በምርኮ የተገኙ የጦር ምርኮኞች ነበሩ። በ1521 ዓ.ም. ኢትዮጵያ የነበረው ፖረቱጋላዊው ሚሲዮን ፍራንቸስኮ አልቫርሽ እንደሚገልጸው በመሃፉዝና ልብነ ድንግል መካከል የተደረገው የ1517ቱ ጦርነት ወቅት ብዛት ያለቸው

37 Awegichew Amare (2021), “The Imperial Traditions…..”, p. 448.

38 “ወይዘፍኑ፡ በበ፡ ልሳነ፡ ብሔሮሙ” (በሀገራቸው ቋንቋም ይዘፍኑ ነበር)፤ J. Perruchon (1893) (tran), *Les Chroniques de Zara Ya'eqob et de Bae'eda Maram rois d'Ethiopie* (Paris: Emile Bouillon), p. 36.

39 René Basset (1897-1909) (ed/tran) *Histoire de la Conquete de l''Abyssinie: (XVI siecle) par Chihab Eddin Aḥmed ben ʿAbdel Qader*, II vols. (Paris: Ernest Leroux) (text); Merid Wolde Aregay (1971), “Southern Ethiopia and the Christian Kingdom…..,pp. 138-139.

ክርስቲያን ወታደሮች ንጉሱን ከድተው ለሙስሊሙ ጦር መሪ ወግነዋል።[40] በ1520ዎቹ ብዛት ያላቸው የክርስቲያን የፖለቲካ አመራሮችና የጦር መሃንዲሶች ከኢማም አህመድ ኢብራሂም ጋር በመሆን የክርስቲያኑን መንግስት ጦር ወግተዋል። በ1543 ዓ.ም. በተደረገው የወይና ደጋ ጦርነት ወቅትም የበር ሰአዳዲን ጦር ሰራዊት ሲሸነፍ ከተማረኩት ውስጥ የክርስቲያኑን መንግስት የከዱ ክርስቲያን ወታደሮች ነበሩ።[41]

በ16ኛው መ.ክ.ዘ. አጋማሽ ላይ የኢትዮጵያ መንግስት የሰራዊት ግንባት ግዙፍ ጦር ሰራዊት እንዳሰባሰበ አረብ ፋቂህ ይነግረናል። አፄ ልብነ ድንግል በ1529 ዓ.ም. 16,000 ፈረሰኛ እና 200,000 እግረኛ ሰራዊት ነበረው። ይህም ከትግራይ፣ አገው፣ ጎጃም፣ በጌምድር፣ አንጎት፣ ቀዳ እና ምድረ-ገኝ የተውጣጣ ነበር።[42] በአፄ ገላውዲዎስ ዘመን (1540-1559 ዓ.ም.) የውጭ ዜጎች የኢትዮጵያ ሰራዊትን ተቀላቅለዋል። ከክርስቶፎር ደጋማ ጋር የመጡ ፖርቱጋላዊያን የነፍጥ ጥቅም ለመጀመሪያ ጊዜ በስፋት እንዲስፋፋ አድርገዋል። የአውሮፓውያንን የእግረኛ ጦር ውጊያ ስልቶችንም ለኢትዮጵያ ጦር ሰራዊት አስተምረዋል።[43]

አፄ ሰርፀ ድንግል የተለያዩ ክፍሎች ያሉት ጦር ሰራዊት ነበረው። በታሪክ ሰነዶች ላይ አዳል መብረቅ፣ ጃን አሞራ፣ ስሉስ ኃይሌ፣ በድል ፀሃይ፣ ጊዮርጊስ ሃይሌ ወዘተ ተጠቅሰዋል። ከዚህ በተጨማሪም አቁት ዠርር፣ አረጓ ጨዋ፣ መሪር፣ ግርሜ፣ ቁርባን፣ ወድ ጎዳር (ወድ ጎዳር-ወታደር?)፤ የኦሮሞ ክፍል የሆነው ጨዋ እንዲሁም የቱርክ እና የመለሳይ ጦር ክፍሎች ነበሩት። የቱርክ ክፍሎች ናር፣ ትሙር እና ኤርማግ በመባል ይታወቃሉ። ከባሪያዎች የተሰራው የጦር ክፍል ደግሞ አግብርት (ባሮች) ይባላል። ይሁንና በክፍለ ዘመኑ ማብቂያ ወሳኝ የኢትዮጵያ መንግስት የጦር ክፍል መሆን የቻለው ቁርባን ነው።[44]

ከአፄ ዘድንግል ግዙፍ ጦር ሰራዊት መለከ ሐራ (የንጉስ ጦር) ቀጥሎ በአፄ ሱስንዮስ ዘመን ብዛት ያላቸው የኦሮሞ ተወላጅ ወታደሮች የኢትዮጵያን ጦር ሰራዊት ክፍሎች

---

40 C.F. Beckingham and G.W.B. Huntingford (1961) (eds/tran), *The Prester John of the Indies: A True Relation of the Lands of the Prester John, Being the Narrative of the Portuguese Embassy to Ethiopia in 1520* (Cambridge: Cambridge University Press for the Hakluyt Society), p. 347.

41 R.S. Whiteway (1902) (ed/tran), *The Portuguese Expedition to Abyssinia in 1541-1543* (London: the Hakluyt Society), pp. 85, 94.

42 René Basset (1897-1909) (ed/tran) *Histoire de la* Conquete…..pp. 34, 55.

43 Andreu Martinez (2007), "Dias, Ayres," *Encyclopaedia Æthiopica*, II, pp. 149-150; Richard Pankhurst and Andreu Martinez d'Alos Moner (2007), "Military Units", p. 431.

44 Carlo Conti Rossini (1961) (ed/tran), *Historia regis Sarṣa (Malak Sagad)…..*; Richard Pankhurst and Andreu Martinez d'Alos Moner (2007), "Military Units" p. 431; Awegichew Amare (2021), "The Imperial Traditions…..", pp. 402-427.

ተቀላቅለዋል። አፄ ሱስንዮስ ከንግስና በፊት በሸዋ በነበረ ወቅት ከቱለማ፣ ባርቱማ፣ ማጫ (ሜጫ)፣ ቦረን እና ሊበን ተወላጅ ወታደሮች ነበሩት። የጭሌሃ፣ አቦ፣ ጭሌሃ ገላን፣ ጃዊ እና ሆከ ነገዶች የክርስትያኑን ግዛት-አፄ ሰራዊትን ሲቀላቀሉ ብዛት ያላቸው የኦሮሞ ተወላጆች የሱስንዮስን ኮከብ፣ ጨረቃ እና ሄኖክ የተባሉ ጨዋዎችን እንዲቀላቀሉ በንጉሱ ተመልምለዋል። ከኦሮሞ ሰራዊት ብቻ የተውጣጣም ጨዋ በንጉሱና የግዛት ገዢዎች እዝ ስር ተሰርቷል።[45]

## የጨዋ ጦር ሰራዊት ሰፈራ

በመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ የጦር ሰራዊት ላይ ምርምር ያደረጉት አለቃ ታየ፣ መርእድ ወልደ አረጋይ፣ ሪቻርድ ፓንክረስት፣ ደረሰ  አየናቸውና አንድሪው ማርቲኔዝ ስለ ጨዋ ሰራዊት ጠቃሚ እውቀት ያጋሩናል። በዘመኑ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር ሰራዊት መጠሪያ ጨዋ ይባል ነበር። በተለያየ ክፍሎች የተደራጁ ወታደሮች ሰራዊት ሐራ እና ጭፍራ በመባል ይጠሩ ነበር።[46] ይህ የጨዋ ሰራዊት ስያሜና አደረጃጀት በምሁራኑ ክርክር ተደርጎበታል። አለቃ ታየ እንደሚነግሩን ወታደሮችን በተለያዩ ቦታዎች ማስፈር "ጨዋ ስሪት" ተብሎ ይታወቃል።[47] ጨዋ የሚለው "የጨዋ ልጅ" በሚለው ሀረግ ውስጥ ጥቅም ላይ ሲውል ትርጉሙም መልካም፣ ሽጋ ወይም ስሪቱ የሰመረ የሚል ይሆናል። ይህም በተለይ "ባሪያ" ከሚለው በተቃርኖ ያስቀምጠዋል።

ይሁንና ዘለግ ያለው የጨዋ ትርጉም ከወታደራዊ ሰራዊት ጋር የተያያዘ ነው።[48] ጨዋ የሚለው ቃል ሴዋ ከሚለው ስም የመጣ ሲሆን ትርጉሙም "ምርኮኛ" የሚል ሲሆን ይህም ከጦር ምርኮ ጋር ያገናኘዋል።[49] የኋላ ኋላ ሴዋ ወደ ጨዋ ተለውጦ ጥቅም ላይ የዋለው በአፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመን ጀምሮ እንደሆነ ይገመታል።[50] በዚህ ወቅት ጨዋ የሚለው ትርጉም ከምርኮኛ ወደ "ነፃ ሰው" ሲቀየር የውትድርና ሙያም ያሳየውን ማህበራዊ እድገት

45 Francisco Maria Esteves Pereira (1892) *Chronica de Susenyos, rei de Ethiopia* (Lisboa: Imprensa Nacional); Richard Pankhurst and Andreu Martinez d'Alos Moner (2007), "Military Units", p., p. 431; ከሸዋ እስከ ደንቀዝ የአፄ ሱስንዮስ እና የኦሮሞ ግንኙነትን፤ የትስስር ሂደቶችንና ዉጤቶችን ለመረዳት ይህንን ተመልከት። Awegichew Amare (2021), "The Imperial Traditions…..", pp. 464-509.

46 Richard Pankhurst and Andreu Martinez d'Alos Moner (2007), "Military Units", p. 431.

47 Taye Gebremariam (*aläqa*) (1922 E.C.) *Yäʾityopya Ḥəzb Tarik* [A History of the People of Ethiopia] (Asmera: Swedish Mission), p. 17.

48 Donald Crummey (2007) "Čäwa," *Encyclopaedia Æthiopica*, I, p. 703.

49 Deresse Ayenachew (2020), "Territorial Expansion and Administrative Evolution under the "Solomonic" Dynasty," in Samantha Kelly (2020) (ed). *A Companion to Medieval Ethiopia and Eritrea* (Netherlands, Leiden: Brill Publishers), p. 77.

50 Merid Wolde Aregay (1997), "Military Elites in Medieval …..", p. 48.

ያመለክታል።[51] አልቫርሽ በበኩሉ ጨዋን "ነፍጥ ያነገቡ ወንዶች" ብሎ ተርጉሞታል። "He is head over fifteen thousand men at arms, whom they name chavas (sic)" (ሀምሳ ሺ የሚደርሱ፤ ነፍጥ ያነገቡ፤ እነርሱ ጨዋ የሚሏቸውን ሰዎች ይመራል)።[52]

የጨዋ ሰራዊት አደረጃጀት ታሪካዊ መነሻ በአግባቡ አይታወቅም። አንዳንድ ጥናቶች ከ1270 በፊት እንደተተገበረና የሰለሞናዊ ነገስታት መሰረታዊ የሰራዊት አደረጃጀት ስርዓት እንደነበር ይጠቁማሉ። ምሁራን እንደሚስማሙት የጨዋ ሰራዊት ማስፈር የተጀመርው ከአፄ ይኩኖአምላክ ዘመን መንግስት ጀምሮ ነበር።[53] በዋናነት የሚሰፍርውም ለጦርነት፣ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እና ለህዝብ ደህንነት ፋይዳ ባላቸው ግዛቶች ላይ ሲሆን ለቆላማና ከፍተኛ ተራሮች መተላለፊያዎቸ ቅርበት እንዲኖረው ይደርጋል።[54] ይህም የጥፋት እንቅስቃሴን ለመግታት እንዲሁም አማካይ ቦታ ላይ በመሆን ለስምሪት በሚመች ቦታ ለማስያዝ ነበር። ይህ የጨዋ ሰራዊት የስሪት ታሪክ ኢትዮጵያ የግዛት አንድነቷን ለማስጠበቅ ለዘመናት የተጠቀመችው ወታደራዊ ብሎም አስተዳደራዊ የአሰራር ስርዓት ነበር።

በተለያዩ ግዛቶች የሚሰፍረው የጨዋ ሰራዊት የተለያዩ ስያሜዎች የሚሰጡት ሲሆን ስም አሰጣጥ የተጀመረው በአፄ አምደ ፅዮን ዘመነ መንግስት ይመስላል። የስያሜዎቹ መነሻ ብዙ ቢሆንም በዋናነት ግን ሰራዊቱን ባደራጀው ንጉሰ ስም፣ በሰፈሩበት አካባቢ እንዲሁም አልፎ አልፎ በሰራዊት የነገድ ማንነት ነበር። የዘላን፣ ጋፋትና የማያ ስሞች የነገድ ስምን ከግምት ያስገባ ሲሆን ይህ ግን በብዛት የሚመርጥ ሆኖ አይገኝም። በአፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመን የነበሩት ስሞች ከፍ ያለ ሃይልን የሚዘግቡ ነበሩ። ለምሳሌ በድል መብረቅ፣[55] በድል መስቀል፣ በድል ደመና፣[56] በፀር ሾተል፣[57] በድል ድብ[58] ወዘተ በዜና መዋእሉ ተጠቅሰዋል። በአዳል አምባ (በአዳል ተራሮች ውስጥ)፣ ደመና አዳል (የአዳል ደመና) ወዘተ ደግሞ አካባቢን የሚጠቁሙ ነበሩ።[59] ለየት ባለ መልኩም በእንስሳት ስም የሚጠሩም ነበሩ። ጃን

51 Deresse Ayenachew (2020) "Territorial Expansion and Administrative Evolution…..", p. 77.

52 Henry Edward John Stanley (1881) (ed/tran), *Narrative of the Portuguese Embassy to Abyssinia During the Years 1520-1527 by Father Francisco Alvarez* (London: Printed for the Hakluyt Society), p. 53.

53 Donald Crummey (2007) "Čäwa," p. 703.

54 Merid Wolde Aregay (1997), "Military Elites in Medieval …..", p. 48.

55 J. Perruchon (tran) (1893), *Les Chroniques de Zara Ya'eqob*…..pp. 31, 35.

56 ዝኒ ከማሁ።

57 ዝኒ ከማሁ፤ ገፅ፤ 19, 22, 31, 35.

58 ዝኒ ከማሁ፤ ገፅ፤ 45.

59 ዝኒ ከማሁ።

አሞራ፣ በድል ድብ እና በሽር አሞራ ይጠቀሳሉ።[60] አንዳንዶቹ ስያሜዎችም ለዘመናት የሚዘልቁ ሲሆን ታሪካዊና እድሜ ጠገብ ሰራዊቶች ስያሜያችውን ሳይቀይሩ መቀጠላቸው የተለየ ዝና እዲኖራቸው አድርጓል። ብዛት ካላቸው የሰራዊት ስያሜዎች በጊዜ ሂደት ደብዛቸው የጠፋም አሉ። ይህም በተለየ በንጉሱ ስም የተደራጁት ሲሆኑ ከንጉሱ ሞት በኋላ ስማቸውን ይቀይራሉ።

ከ14ኛው መ.ክ.ዘ. ጀምሮ እየሰፋ የመጣው የኢትዮጵያ ግዛትና ድንበር የጨዋ ሰራዊቱን ቁጥር ማደግና በተለያዩ ግዛቶች መስፈር አስገድዷል። በአንድ የስምሪት ቀጠና የሚሰፍረው የጨዋ ሰራዊት ብዛት በግልጽ አይታወቅም። ይሁንና አዛዦቻቸው በሚመሩት የሰው ሀይል ብዛት ተቀራራቢ መላ ምት ማስቀመጥ ይቻላል። እነዚህም የሰራዊቱ የተለያዩ ክፍሎች አዛዦች የተለያየ መጠሪያ አላቸው። አዝማች፣ ደጃዝማች፣ ራስ፣ ፊታውራሪ፣ ባላምባራስ፣ አዛዥ እና ባሻ ረዘም ላለ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋሉ ናቸው። የሚያዙት የሰራዊት ቁጥርም የተለያየ መጠን ያለው ነበር። ከፍተኛ ቁጥር ያለውን የጨዋ ሰራዊት የሚያዘው ራስ ሲሆን እስከ 40,000 ይደርሳል። ደጃዝማችና ፊታውራሪ እያንዳንዳቸው እስከ 10,000 ሰራዊት ሊኖራቸው ይችላል። ዝቅተኛ የወታደራዊ ስልጣን ያላቸው የጦር አዛዦች ከ2000 እስከ 5000 የሚደርሱ የጨዋ ወታደሮችን ይመራሉ።[61]

ይህ የጨዋ ሰራዊት በተሰማራበት ግዛት ሲሰፍር በአለቃ ታየ አገላለፅ "በማያውቀው ህዝብ ላይ ጨዋ ሆነ" ይባላል።[62] ሰራዊቱ ከሰፈረበት አካባቢ ተወላጆች ጋር የሚያደርገው መስተጋብር በተሰጠው ግዳጅ ጋር የተቆራኘ ነው። ለምሳሌ የንግድ መስመር ተከትሎ የሚሰፍሩ ወታደሮች በአካባቢው ተወላጆች ጋር በመተባበር ሽፍቶችንና የጥፋት ቡድኖችን ይጋፈጣሉ። ይህ የአላማ አንድነት ለበለጠ ትስስር ምክንያት ይሆናል። የንግድ መንገዶችንና ገበያዎችን ደህንነት ለመቆጣጠር የሚደረግ የጨዋ ሰራዊት አደረጃጀቶች የኢትዮጵያን መንግስት ወታደራዊ ባህሪ እንዲላበስ ካደረጉ ምክንያቶች አንዱ ነው።[63]

የጨዋ ሰራዊት በሰፈረበት አካባቢ ከሚኖረው ማህበረሰብ ጋር የነበረው ግንኙነት ለረጅም ዘመናት የተካሄደ ነው። ከአፄ አምደ ፅዮን ጀምሮ ሁለት ስርአቶች ነበሩ። በጦርነት ወቅት ለሰራዊቱ ቀለብ የሚሰፍረውና ስንቅ የሚያቀርበው ሰራዊቱ የሚያልፍበት ወይም የሚያርፍበት አካባቢ ህዝብ ነው። ሁለተኛው ስርአት የሚሰራው ይህ ሰራዊት ለረጅም ጊዜ በአንድ ቦታ የሚሰፍር ከሆነ ነው። ይህ ሲሆን ለጨዋ ሰራዊቱ ጉልት ይጎለታል።

60 ዝኒ ከማሁ፤ ገፅ፤ 143, 148; Richard Pankhurst and Andreu Martinez d'Alos Moner (2007), "Military Units", pp. 432-33.

61 Richard Pankhurst and Andreu Martinez d'Alos Moner (2007), "Military Units", pp. 432-33.

62 Taye Gebremariam (1922 E. C) *Yäʾityopya Ḥəzb Tarik.*, p. 17.

63 John Markakis (1968) "An Interpretation of Political Tradition in Ethiopia," *Présence Africaine, Nouvelle série*, LXVI, pp. 88-89; Awegichew Amare (2021) "The Imperial Traditions…..", p. 137.

ይኸውም የአካባቢው ማህበረሰብ ለጠባቂው የጨዋ ስራዊት ወጭ የሚሸፍንበት በግብር ላይ የተመሰረተ ስርዓት ነው።[64]

ማህበረሰቡ ለሰፈረው ጨዋ የሚያደርገው የድጋፍ አይነት በምሁራን ጥናቶች መግባባት አልተደረሰበትም። ፈረንሳዊቷ የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪ አናይስ ቪዮ ለጨዋ ሰራዊቱ የምግብ፣ የመጠለያና ሌሎች ወጪዎችን የመሸፈን ኃላፊነት የህዝቡ እንደነበር ትገልጻለች። [65] መርዕድ በበኩላቸው ነፃ የጉልበት ስራ ለጨዋ ሰራዊት መስጠት የማህበረሰቡ ግዴታ እንደነበር ጽፈዋል።[66] የሆነ ሆኖ ይህ የጨዋ ሰራዊትን በማስፈር፤ ለመተዳደሪያው ጉልት በመጎለትና ማህበረሰቡ ሰራዊቱን የሚደግፍበት ስርዓት ማበጀት የዝነኛው የጉልት ስርዓት ዘ-ፍጥረት እንደሆነ ይታመናል።

በጨዋ ሰራዊትና በአካባቢው ማህበረሰብ መካከል የተሰራ የትብብር ስርዓት ጉልህ የባህል፣ ማህበራዊ ህይወት፣ የፖለቲካ ልምምድና ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰቦች ልውውጥ ፈር-ቀዳጅ ነበር። የጨዋ ሰራዊት አባላት በሰፈሩበት አካባቢ ካለ ማህበረሰብ ጋር በጋብቻ ይተሳሰራሉ። ይህ በክርስቲያን ወታደሮችና ክርስቲያን ባልሆኑ ማህበረሰቦች መካከልም ይመዘገባል። ለአብነትም የአፍሮ አይገባ ጨዋ ሰራዊት ሰፍሮበት ከነበረው የምስራቅ ሸዋ ሙስሊምና ክርስቲያን ማህበረሰብ ጋር እንዲሁም ከሃረርና አዳል ከመጡ ተፈናቃዮች ጋር በጋብቻ ተሳስረዋል።[67] በዚህ ሂደት በምን ደረጃ የኃይማኖት ልውውጥ እንደተደረገና የአካባቢው ማህበረሰብ የጨዋ ሰራዊቱን ኃይማኖት፣ ባህልና ቋንቋ እንደተቀበለ በሚገባ ለመሰነድ የታሪክ መረጃዎች በቂ አይደሉም። ያሉትን የታሪክ ሰነዶች በማገላበጥ ጣሊያናዊው የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪ ካርሎ ኮንቲ ሮሲኒ እንደሚነግረን ብዛት ያላቸው የጨዋ ወታደሮች በማህበረሰቡ ተውጠው ባህል፣ ቋንቋና ኃይማኖታቸውን ቀይረው በመስተጋብር ቀልጠዋል።[68] ከመደበኛ ጨዋ ሰራዊት ሳሉ በሰሩት ወንጀል ከቅጣት ለመሸሽ ወይም ወንጀል የሰሩ ወታደሮች ወደማይታወቁበት ቦታ በመሄድ

64 Richard Pankhurst and Andreu Martinez d'Alos Moner (2007), "Military Units", pp. 432-33.

65 Anaïs Wion (2020), "Medieval Ethiopian Economies: Subsistence, Global Trade and the Administration of Wealth," in Samantha Kelly (2020) (ed), A *Companion to Medieval Ethiopia and Eritrea* (Netherlands, Leiden: Brill Publishers), p. 409.

66 Merid Wolde Aregay (1997), "Military Elites in Medieval …..", p. 80.

67 Merid Wolde Aregay (1971), "Southern Ethiopia and the Christian Kingdom…..", p. 435.

68 Carlo Conti Rossini (1914), *Studi su Popolazion Dell'Etiopia* (Rome: Casa Editrice Italiana), p. 853.

ጠፍተው ይቀራሉ።[69] በተጨማሪም የወታደሮች መስፈር አዳዲስ የባህል የፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰቦች ወደ አዲስ የተቆረቆሩ አከባቢዎች እንዲዛመቱ አብይ ምክንያት ሆነዋል። የጉልትና ርስት ስርአት እንዲሁም የክርስትና ኃይማኖት መስፋፋትም ከዚሁ የጨዋ ሰራዊት እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ የታሪክ ሂደት አካል አለው።[70]

በጨዋ ሰራዊትና በማህበረብ መካከል ያለው ትስስር እንዲጠናከር ከሚያደርገው ምክንያቶች አንዱ የሰራዊቱ ለረጅም ዓመታት በተመሳሳይ ቦታ መስፈር ነው። በዚህም የተነሳ የአካባቢው ተወላጅ ከሰፈረው ሰራዊት ጋር በጋብቻ፣ በጓደኝነት እና በቤተሰብ ትስስር መፍጠር ችለዋል። ይህም ወታደሮቹን እንደመጤ እና ሰፋሪ የማየት አዝማሚያ እንዳልነበረ ይጠቁማል። በሂደትም መንግስት ማህበረሰቡ ለሰራዊቱ እንዲያደርጉ ብሎ ያስቀመጣቸው አስገዳጅ ሃላፊነቶች እንዲለዝቡና የተለሳለሰ ግንኙነት እንዲጎለብት አድርጓል። በዚህ ውስብስብ ትስስር የተነሳም ከተለያዩ የብሄር፣ ሀይማኖት፣ ቋንቋና አካባቢ ከመጡ የጨዋ ሰራዊትና ከአካባቢው ማህበረሰብ ውህደት የተገኙ ወታደሮች እና የጦር አዛዦችን ማንነትና ሚና በታሪክ መረጃዎች ላይ እናገኛለን።[71] ከማህበረሰቡ ጋር ጥብቅ ትስስር በማድረጉ የጨዋ ሰራዊቱ ከህዝብ በመወገን አንዳንድ አመፃዎችን የተቀላቀለበትና የመራበት አጋጣሚም አለ።

ለረጅም አመታት በአንድ አካባቢ መስፈር የጨዋ ሰራዊቱ ከማህረሰቡ ጋር ያለውን መስተጋብር እንዳጠነከረው ሁሉ የሰራዊቱ ከቦታ ቦታ በተደጋጋሚ የሰፈራ ቦታ መቀየሩ የራሱ አስተዋፅኦ ነበረው። ይህም ሰራዊቱ ከተለያዩ ማህበረሰቦች ጋር ንክኪ እንዲኖራቸው አድርጓል። የኢትዮጵያ ግዛት አካል ሆኖ ያልሰፈሩበትና ያልደረሱበት ቦታም አልነበረም። ለዚህ ጥሩ አስረጂ የሚሆነው የኢትዮጵያ ታማኝ የጦር ሰራዊት አባል በመሆን ያገለገሉትን የማያ ጨዋ ነው። ማያዎች አርብቶ አደር የነበሩ ሲሆን በምድረ ወጅ ከላይኛው አዋሽ በስተደቡብ እና ምእራብ ክፍል ይኖሩ ነበር። በ14ኛው እና 15ኛው መ.ክ.ዘ. የራሳቸው መሪ የነበራቸውና ክርስትናንም ሆነ እስልምናን ያልተቀበሉ ነበሩ። ይሁንና የኢትዮጵያ ክርስትያን ነገስታት ለውትድርና ከሚመርጧቸው ግምባር ቀደም ነበሩ።

በ1448/49 ዓ.ም. ማያዎች በአፄ ዘርአ ያዕቆብ ዕዝ ጨዋ ተብለው በኤርትራ ሰፈሩ። ለሚቀጥሉት ሁለት መቶ አመታትም ጠንካራ የውትድርና ብቃታቸው፤ በመርዛማ ቀስቶቻቸው የሚታወቁ ሆኑ። በአፄ ዘርአ ያዕቆብ የሰፈራ ቦታ ለውጥ ካደረጉ በኋላም በሃረር፣ በአፋር፣ በእብናት (በጌምድር) እንዲሁም በጣና ሃይቅ ዙሪያና በአቸፈር ሰፍረው ነበር። ይህም በተለያዩ ነገስታት የተለያየ የስፍራ ቦታ እንደተሰጣቸው እና በጨዋነት እንደተሰሩ ይጠቁማል። ይህም ክርስትናን ባይቀበሉም ከክርስቲያኑ ነገስታት ጋር ወዳጅነት እንደነበራቸው ይጠቁማል። ይህ በግዳጅ የሃይማኖት ለውጥ ላይ ያልተመሰረተ ግንኙነት

69 ከጎንደር ክፍለ ሀገር ጠፍተዉ በቦረናና ሲዳሞ ቀልጠው ስለቀሩ ወታደሮችና ሽፍቶች ታሪክ ይህንን ተመልከቱ። A.W. Hodson (1927), *Seven Years in Southern Abyssinia* (London), pp. 70-71.

70 Donald Crummey (2007) "Čäwa," p. 703.

71 Awegichew Amare (2021), "The Imperial Traditions…..".

የወቅቱን ወታደራዊ አደረጃጀት መልኮች ይጠቁማል። ማያዎች ከሰፈሩባቸው ስፍራ መቀያየር የተነሳ ከብዙ ማህበረሰቦች ጋር ንክኪ እንደነበራቸው እንገነዘባለን። በ16ኛው መ.ክ.ዘ. ከበር ሰአዳዲን መሪ ወታደሮች እና ከኦሮሞዎች ጋርም ይተዋወቃሉ። በ17ኛው መ.ክ.ዘ. የአፄ ሱስንዮስ ወታደር ሆነው በንጉሱ ይሁኝታ በጎጃም መሬት ተሰጥቷቸው በአቸፈር ከጣና ሃይቅ ደቡብ ምዕራብ ክፍል መስፈር ችለዋል።[72]

የጨዋ ወታደሮች በሰፈሩበት አካባቢ ጋር ያላቸውን መስተጋብሮች ለማጥናት የሰፈሩበትን አካባቢና የባህልና ሁኔታ እንዲሁም ከሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ወደ ደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅና ደቡብ ምእራብ የሰፈረውን ጨዋ አሰፋፈር መረዳት ያስፈልጋል። የባህረ ነጋሹ ግዛት የነበረው ከመረብ ወንዝ በስተሰሜን ያለውን ክፍል ማህበረሰብ በፃር ወጀት ከተባለው ጨዋ ሰራዊት ጋር ለረጅም አመታት ይተዋወቃል።[73] በትግሬ መኮንኑ ግዛት የማያዎች እና የትግሬ ጨዋ የሰፈረ ሲሆን ይህም ሰራዊት ከተከዜ ወንዝ በስተሰሜን እስከ ምፅዋ እና አርቂቆ ድረስ ካለው ማህበረሰብ ጋር የረዘመ ግንኙነት ያላቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ታላቁ የአንጎት ግዛት የዝነኛው ጃን አሞራ ጉልት ነበር። ይህ ጨዋ ለአፄ አምደ ፅዮን ወታደሮች የተዜመ የሙገሳ ግጥም ላይ ተጠቅሷል። ስሙም ከአንጎት ግዛት ጋር ተያይዞ ይነሳል።[74] ግዛቱም የክርስቲያን አማራዎች ምድር እንደነበረ መርእድ ይነግሩናል።[75] በቀዳማዊ አፄ ባዕደ ማርያም ዘመን (1468-1478 ዓ.ም.) የንጉሱ ጨዋ ሆኖ በጠለምት ተሰርቶ ነበር። ይህ ማለት በአፄ ዘርአ ያዕቆብ ዘመን በጠለምት የተተከለው የዶባ ሽፍቶች ከደቡብ ምስራቅ ትግራይ በመነሳት ህዝቡ ላይ አደጋ እንዳይጥሉ ለመከላከል የተሰራ ስምሪት ነበር ማለት ነው። የጃን አሞራና የዶባ ትንቅንቅ እስከ 16ኛው መ.ክ.ዘ. ድረስ የቀጠለ ሲሆን ረዘም ላለ ጊዜ በአንጎት፣ በጠለምት እና በትግራይ ካሉ ህዝቦች ጋር አብረው እንደኖሩ ያስረዳል። የኋላ ኋላ በ16ኛው መካከለኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ (1554-62) ከኦሮሞ ጦረኞች ጋር ፍልሚያ ካደረጉ በኋላ በምን ደረጃ በጨዋነት እንደቀጠሉ የታሪክ

72 Merid Wolde Aregay (1971), "Southern Ethiopia and the Christian Kingdom…..", pp. 32, 83, 96; Carlo Conti Rossini (1961) (ed/tran), *Historia regis Sarṣa (Malak Sagad)*….., p. 52; Francisco Maria Esteves Pereira (1892), *Chronica de Susenyos*….., pp. 146, 210; James Quirin (2007), "Maya" *Encyclopaedia Æthiopica*, pp. 887-889.

73 Deresse Ayenachew (2020), "Territorial Expansion and Administrative Evolution…..", p. 79.

74 G.W.B. Huntingford (ed/tran) (1965), *The Glorious Victories of Amda Seyon*….., p. 129.

75 Merid Wolde Aregay (1971), "Southern Ethiopia and the Christian Kingdom…..", p. 32.

ሰነዶች አይነግሩንም። ምናልባት ወደሌላ ቦታ ተዘዋውረው ሊሆን ይችላል።[76] ከጃን አሞራ ጋር ተያይዞ የሚነሳው የጃን ቀንጠፋ (ጃን ቃጥፋ) ጨዋ ነው። ይህ ጨዋ በአፄ ዘርአ ያዕቆብ ዜና መዋእል ላይ ተመላክቷል።[77] በደረሰ አየናቸው ጥናት መሰረት ጃን ቃጥፋ ከትግራይ ጨዋ፣ ጃን አሞራ፣ ጃን ፀገና፣ ዳዊት አምባ ጋር በመሆን በዶባ አርብቶ አደሮችና በከፍተኛ ተራሮች በሚኖረው አርሶ አደር ማህበረሰብ መካከል የተሰራ ነበር።[78]

የመካከለኛው እና የሰሜን ምእራብ ግዛቶችም ከተለያዩ ማንነቶች በተደራጀው የጨዋ ሰራዊት ይጠበቁ ነበር። የበጌ ምድር ጨዋ፣ የአንጎት ጨዋ፣ የአማራ ጨዋ እና የጎጃም ጨዋ በተጠቀሱት ግዛቶች ጉልት ተጎልተው በጨዋ ሰራዊትነት ሰፍረውም ነበር።[79] እነዚህ ግዛቶች ውስጥ የተለያየ የባህል ማንነት ያለው ማህበረሰብ መኖሩና በመስተጋብር እየተሳሰረ በመሄዱ ለጨዋ ሰራዊቱ እንግዳ ሊሆንበት አይችልም። የአካባቢውን ስም መያዛቸውም ስሪታቸው ለረጅም አመት የዘለቀ መሆኑን ይጠቁማል።

በዳሞት የጃን በድል ጨዋ ሰራዊት ሰፍሮ ነበር። ይህ ጨዋ በአፄ ዘርአ ያዕቆብ እንደተመሰረተ ይታወቃል። ምናልባትም የጃን ሀፃና ወደ አዳል መክዳት ተከትሎ በንጉሱ ተሰርቶ ሊሆን ይችላል። በአፄ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል መሰረት ጃን በድል የቦታ ስም ሆኖ ይገኛል። ንጉሱም የሊበን ኦሮሞዎችን አስፍረውበት ነበር። የዚህ ጨዋ ሰራዊት የአባይ ገባር በሆነው የበር ወንዝ አጠገብ በዳሞት ተሰርቶ ለረጅም አመታት በማገልገሉ የሰራዊቱ ስም የቦታው መጠሪያ ሆኖ መቅረቱን ይጠቁማል።[80]

በሸዋ የአዋሽ ወንዝን ተከትሎ የአካባቢዉን ስም እና የነገድ ስም የያዙ የጨዋ ክፍሎች ሰፍረዋል፡፡ በቀጠናዉም የሸዋ ጨዋ፣ በፈጠጋር የፈጠግርና የማያ ጨዋ፣ እና የጋፋት ጨዋ የሰፈረ ሲሆን በደቡብ ምዕራብ ሸዋ የገንዝ ጨዋ ሰፍሯል፡፡ በተለያዩ የሸዋ፤ ፈጠጋር፤ ኢፋትና ዳሞት ግዛቶች በአፍሮ አይገባ፤ ጊዮርጊስ ሃይሌ እና ዳሞት ሃዳሪ ጨዋ ሰራዊቶች ይጠበቁ ነበር፡፡ በሃድያ የሃድያ ጨዋ፣ በወጅ የወጅ ጨዋ ሲሰፍር በባሊ የባሊ ጨዋና የተናጭ ጨዋ ሰራዊት ሰፍሮ ነበር፡፡ በደዋሮና አዳል ደግሞ ለረጅም ዓመታት በጨዋነት የተሰሩት እነ አዳል ሙብረቅና በድል ድብ ይገኙበታል፡፡ አዳል ሙብረቅ በአፄ ዘርአ ያእቆብ ዜና መዋእል ላይ በአዳል ሙብረቅ ተብሎ ሲጠራ አባ ባሕሬ በኦሮሞ ዜና መዋዕል ላይ አዳል ሙብረቅ ብለው ይጠሩታል፡፡[81] በአፄ አምደ ፅዮን ዜና መዋእል የአዳል ሙብረቅ የጦር

---

76 Denis Nosnitsin (2007), "Ğan Amora," *Encyclopaedia Æthiopica,* pp. 682-683.

77 J. Perruchon (tran) (1893), *Les Chroniques de Zara Ya'eqob…..,* pp. 136, 148.

78 Deresse Ayenachew (2020), "Territorial Expansion and Administrative Evolution…..", p. 79.

79 Deresse Ayenachew (2020), "Territorial Expansion and Administrative Evolution…..", p. 79.

80 Sevir Chernetsov (2007), "Ğan Bädəl," *Encyclopaedia Æthiopica,* p. 683.

81 J. Perruchon (tran) (1893), *Les Chroniques de Zara Ya'eqob*…..p. 31; Bahrey (1954), "The History of the Galla", in C. F. Beckingham and G. W. B.

ልሂቃኖች ይሞገሳሉ፡፡ ዣን የሚለው ንጉሱን ለመዘከር ታስቦ ከሆነ የአዳል መብረቅን ጀግንነት ወራሽ ተደርጎ ቀርቧል፡፡ በግጥሙ ላይም አዳል መብረቅ ባላጋራዉን አዳልን አስበርግጎ ወታደሮቻቸዉን ቅስማቸውን እንደሰበረው የሚገልጽ መልእክት ያስተላልፋል፡፡[82] ይህም ኢፋት በአፄ አምደ ፅዮን ከተያዘ በኋላ ደዋሮ የአዳል ሙብረቅ ጉልት ሆነ፡፡[83] ይህ ሰራዊቱ የሰፈረባቸው የተለያዩ አካባቢዎች በሂደት ወደ ከተማነት የተቀየሩ ሲሆን ይህም የመስተጋብር ውጤት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ከአፄ ሰርፀ ድንግል ዘመን ጀምሮ ብዛት ያላቸው የኦሮሞ ተወላጆች የኢትዮጵያን ክርስቲያን ግዛተ-አፄ ጨዋ፣ የተለያዩ የጦር አዛዦችን ጨዋ እና ኢ-መደበኛ አደረጃቶችን ተቀላቅለው በተለያዩ ቦታዎች ላይ ሰፍረዋል። በ1570ዎቹ መጨረሻ ላይ የኦሮሞ ጨዋ ሰራዊት በሰርፀ ድንግል መሪነት ባህረ ነጋሽ ይስሀቅን እና ቱርክን በደባርዋ፣ አዲ ቆሮ እና እንጢጮ በተባሉ ቦታዎች ተዋግቶ ድል አድርጓል። በ1590 ዓ.ም. ተመሳሳይ ግዳጅ ተወጥቷል።[84] ይህም ንጉሱ የኦሮሞ ወጣት ተዋጊዎችን ወደ ሰራዊቱ በመቀላቀል የመጀመሪያው ያደርጋቸዋል። ይህ የጨዋ ሰራዊት በደምቢያ፣ ወገራ፣ ዳህራ እና ሳማ ሰፍሮ ነበር።[85] ይህ ከኦሮሞ ሀይሎች ወታደሮችን የመመልመል እና በተለይ ከአማራው ህዝብ መካከል የማስፈር ባህል እየተለመደ በመሄዱ በጎንደር የነገሱ የኢትዮጵያ ነገስታት ታሪክ አካል ሆኖ ይገኛል። ይህም በተለይ የአማራ እና ኦሮሞ ህዝብን ትስስር መልኮች፣ ሂደቶችና ውጤቶች የሚያሳይ ተጨማሪ የታሪክ ምርምር የሚጠይቅ የታሪክ አካል ነው።

## ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ የመካለኛው ዘመን የጦር ሰራዊት ታሪክ በታሪክ ምሁራን በቂ ትኩረት አላገኘም። ያሉትን ውስን የታሪክ ሰነዶች በመመርመር እንደምንረዳው የጨዋ ሰራዊቱ ከ14ኛው መ.ክ.ዘ. ጀምሮ በአዲስ መልክ ሊዋቀር ችሏል። የሰራዊቱ ማህበራዊ መሰረት ብዝሀነት ያለው ሲሆን ከሰፈረበት ማህበረሰብም ግር ጥብቅ ቁርኝት መስርቷል። በተለያዩ ጊዜያት በተነሱ ተፎካካሪ ሀይሎች ጉዳት ቢደርስበትም የመስተጋብር ውጤት መሆኑ ፈፅሞ እንዳይፈርስ ምክንያት ሆኗል። በዚህም የተነሳ የኢትዮጵያ የግዛት አንድነትና የመንግስት ተቋማት ቀጣይነትን በመጠበቅ ጉልህ አስተቃፅኦ አድርጓል። የሀገሪቱን ማህበረሰብ በማስተሳሰርም ግምባር ቀደም ተዋናይ ነው።

---

Huntingford (eds/tran), *Some Records of Ethiopia, 1593-1646* (London: Hakluyt Society), p. 116.

82 G.W.B. Huntingford (ed/tran) (1965), *The Glorious Victories of Amda Seyon*….., p. 131-132.

83 Merid Wolde Aregay (1997), “Military Elites in Medieval …..”, p. 51.

84 Awegichew Amare (2021), “The Imperial Traditions…..”, pp. 406-427.

85 ዝኒ ከማሁ፣ ገፅ 416.

**ዋቢ መፃህፍት**

Awegichew Amare (2019). "Yä-Oromo Həzb Tarikən Yätänətärasu Yätərəkət Täqarənowoč Lämaläzäb Yähəzbəna Bahəl Mästägabər Tarik Mərmər Mina." [The Role of a History of Interaction and Integration of People and Culture to Bridge Conflicting Narratives in Oromo History]. *Journal of Afroasiatic Languages, History and Culture.* VIIII, II, 2019, pp. 221-245.

Awegichew Amare. (2021). "The Imperial Traditions of the Ethiopian State and the Oromo Factor (XIV-XVIII Centuries)." PhD Dissertation in History, Addis Ababa University.

Bahrey (1954). "The History of the Galla", in C. F. Beckingham and G. W. B. Huntingford (eds/tran). *Some Records of Ethiopia, 1593-1646*. London: Hakluyt Society, pp. 111-29.

Basset, René (1897-1909) (eds/tran). *Histoire de la Conquete de l"Abyssinie: (XVI siecle) par Chihab Eddin Aḥmed ben ʿAbdel Qader*. II vols. Paris: Ernest Leroux. (text).

Beckingham, C.F. and Huntingford, G.W.B. (eds/tran). *The Prester John of the Indies: A True Relation of the Lands of the Prester John, Being the Narrative of the Portuguese Embassy to Ethiopia in 1520*. Cambridge: Cambridge University Press for the Hakluyt Society.

Budge, Ernest Alfred Wallis (1906) (ed./tran), *The Life and Miracles of Takla Hâymânôt in the Version of Dabra Libânôs* (London: rivately printed for Lady Meux).

Caquot, André (1957). "La royauté sacrale en Éthiopie." *Annales d'Ethiopie*. II, pp. 205-218.

Chernetsov, Sevir (2007). "Ǧan Bädəl." *Encyclopaedia Æthiopica*, p. 683.

Conti Rossini, Carlo (1914), *Studi su Popolazion Dell'Etiopia* (Rome: Casa Editrice Italiana).

Conti Rossini, Carlo (ed/tran) (1961-62). *Historia regis Sarṣa Dengil (Malak Sagad). Accedit historia gentis Galla, curante I. Guidi*. II vols., CSCO II ser., III (Paris, 1907), repr. as CSCO XX-XXI, SAe III–IV (Louvain) (text).

Crummey, Donald (2007). "Čäwa." *Encyclopaedia Ǣthiopica.*

Daniel Kibret. 2011. *ʾItyopyawiw Surafi, Yä-Abuna Täklähaymanot Yähəyəwot Tarikəna Asətäwaṣo* (The Ethiopian *Sur'afi*, The Biography and Achievements of *Abunä* Täklähaymanot). Addis Ababa.

Derat, Marie-Laure (2020). "Before the Solomonids: Crisis, Renaissance and the Emergence of the Zagwe Dynasty (Seventh–Thirteenth Centuries)" in Samantha Kelly (ed). *A Companion to Medieval Ethiopia and Eritrea* (Netherlands, Leiden: Brill Publishers), pp. 31-56.

Deresse Ayenachew (2020). "Territorial Expansion and Administrative Evolution under the "Solomonic" Dynasty." in Kelly, Samantha (2020) (ed). *A Companion to Medieval Ethiopia and Eritrea* (Netherlands, Leiden: Brill Publishers), pp. 57-86.

Esteves Pereira, Francisco Maria (1892). *Chronica de Susenyos, rei de Ethiopia.* Lisboa: Imprensa Nacional.

Guidi, Ignazio (1889). Le Canzoni Geez-Amarina in onore di re Abissini.‖ *Rendiconti della Reale Accademia dei Lincei*. series IV, V, Roma, pp. 53-66.

Heran Serke Berhan (2002). "Building Bridges, Drying Bad Blood: Elite Marriage, Politics and Ethnicity in the 19th and 20th Century Imperial Ethiopia." PhD Dissertation, Department of History, Michigan State University.

Hodson, A.W. (1927). *Seven Years in Southern Abyssinia* (London).

Huntingford, G.W.B. (eds/tran) (1965) *The Glorious Victories of Amda Seyon* (Oxford: Clarendon Press).

Hussein Ahmad (1992). "The Historiography of Islam in Ethiopia." *Journal of Islamic Studies*. III, I, pp. 15-46.

John Stanley, Henry Edward (1881) (ed/tran). *Narrative of the Portuguese Embassy to Abyssinia During the Years 1520-1527 by Father Francisco Alvarez*. London: Printed for the Hakluyt Society.

Markakis, John (1968). "An Interpretation of Political Tradition in Ethiopia." *Présence Africaine, Nouvelle série*. LXVI, pp. 79-97.

Merid Wolde Aregay (1971). "Southern Ethiopia and the Christian Kingdom 1508- 1708, With Special Reference to the Galla Migrations and their Consequences." PhD Dissertation. Department of History. SOAS, University of London.

Merid Wolde Aregay (1974). "Population Movements as a Possible Factor in the Christian-Muslim Conflict of Medieval Ethiopia," *Symposium Leo Frobenius; Perspectives of Contemporary African Studies*, pp. 266-281.

Merid Wolde Aregay (1997). "Military Elites in Medieval Ethiopia." *Journal of Ethiopian Studies*, XXX, I, pp. 31-73.

Pankhurst, Richard and Martinez d'Alos Moner, Andreu, (2007). "Military Units." *Encyclopaedia Æthiopica*. V, pp. 430-433.

Perruchon, J. (1893) (tran). *Les Chroniques de Zara Ya'eqob et de Bae'eda Maram rois d'Ethiopie*. Paris: Emile Bouillon.

Phillipson, David W. (2004). "The Aksumite Roots of Medieval Ethiopia." *Journal of British Institute in East Africa*, pp. 77-89.

Quirin, James (2007). "Maya." *Encyclopaedia Æthiopica*, pp. 887-889.

Shiferaw Bekele (1990). "Reflection on the Power Elites of the Wäräšeh Mäsfenate (1786-1853)." *Annales d''Ethiopie*. XV, pp. 157-179.

Taddesse Tamrat (1972). *Church and State in Ethiopia*, 1270-1527. London: Clarendon Press.

Taye Gebremariam (*aläqa*) (1922 E.C.). *Yäʾityopya Ḥəzb Tarik* [A History of the People of Ethiopia]. Asmera: Swedish Mission.

Whiteway, R.S. (1902) (eds/tran). *The Portuguese Expedition to Abyssinia in 154I-1543.* London: the Hakluyt Society.

Wion, Anaïs (2020). "Medieval Ethiopian Economies: Subsistence, Global Trade and the Administration of Wealth." in Kelly, Samantha. ed. A *Companion to Medieval Ethiopia and Eritrea*. Netherlands, Leiden: Brill Publishers, pp. 395-425.

Yates, Brian J. (2002). "Invisible Actors: The Oromo and the Creation of Modern Ethiopia (1855- 1913)." PhD Dissertation, Department of History, University of Illinois.

Yates, Brian J. (2010-2011). "Acculturation in the Däga: Local Negotiations in Amhara/Oromo Relations." *International Journal of Ethiopian Studies*, VI, 11.

*Awegichew Amare Agonafir, PhD*
*Department of History,*
*Gonder University*